ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
**Coalition for Unity and Democracy Party**
**(Kinijit)**
e-mail kil@kinijitinternational.org

KIL_PR_AMH/008
ጥቅምት 14 ቀን 1999

# የምርመራ ኮሚሽኑ ውጤት በታሰሩት ላይ የሚቀርቡት መረጃዎችም ሀሰት መሆናቸውን ያጋልጣል

የግንቦቱን ምርጫ ተከትሎ የኢህአዴግ መንግስት የምርጫ ውጤት ማጭበርበሩ ህዝባዊ ቁጣን ቀስቅሷል:: የሰብአዊና ህገመንግስታዊ መብቶችን በይፋ በማፈኑ ምክንያቶች መሰረታዊ የዜግነት መብቶች በጉልበትና በማናለብኝነት ተጨፍልቀዋል::

በሰኔ ወር፣ በጥቅምት መጨረሻና ህዳር መጀመሪያ አካባቢ ወገን በወገኑ ላይ ሊፈጽም የማይገባውን ጭፍጨፋና አፈና፣ ማሳደድና ማሰር፣ ባሰለፋቸው ልዩ የጦር ኃይል አባላት አማካኝነት፣ የስልጣን ጥማት ባናወዛቸው ባለስልጣናት ትዕዛዝ አካሂዷል:: ከ60,000 በላይ ዜጎች በየቦታው ታስረዋል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች አገር ጥለው ተሰደዋል:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ቆስለዋል፣ አካለ ስንኩል ሆነዋል፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ተገድለዋል::

በወቅቱ በሁለቱ የጭፍጨፋ ወቅቶች መንግስት የሞቱትን ቁጥር ከ80 በታች ሲአደርግ፣ የቆሰሉትን ከሁለት መቶ ያነሰ መሆኑን እየማለና እየተገዘተ ገልጿል:: የኢትዮጵያ ህዝብና ቤቱ የሚቆጥረው ግን በጣም ከፍተኛ ቁጥር ነበር::

ከዓለም ህብረተሰብ በተደረገበት ጫና በወቅቱ ነፃ ያልነበረ የመርማሪ ኮሚሽን በፓርላማው አማካኝነት አቋቁሟል:: ገና ከመጀመሪያው አያያዙ ያላማራቸው የኮሚቴ አባላት ጤንነትን ምክንያት በማድረግ አፈንግጠዋል:: ኮሚቴው የኢህአዴግ ፓርላማ ከመበተኑ በፊት ሪፓርት ማቅረብ ይጠበቅበት ስለነበር፣ ሪፓርቱ የኢህአዴግን ገበና እንዲሸፍንና የተቃዋሚውን ወንጀለኛነት እንዲያከብድ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ጫና ተደርገውበታል::

ምንም እንኳን ኢህአዴግን የሚደግፉ ቢሆኑም በህዝብ ላይ የተፈፀመው በደልና የመንግስት መረን የለቀቀ ውሸት የህሊና ቁስል ስለሆነባቸው የተወሰኑ የኮሚቴ አባላት አገር ጥሎ በመውጣት ሊታፈን የነበረን ሀቅ ይፋ አድርገዋል::

በዚህም መሠረት ኢህአዴግ የሞቱትን ቁጥር ሰማኒያ ቢልም በመረጃ ያረጋገጡት 199 መሆኑን የቆሰሉት ቁጥርም 763 መሆኑን ባዘጋጁት ሪፓርት አጋልጠዋል::

ምንም እንኳን ይህ ቁጥር በማስረጃ በስምና በአድራሻ የተደገፈ ቢሆንም፣ በኮሚቴውና በመንግስት እምነት በማጣታቸው ምክንያት ፊት ለፊት ያልወጡና በደላቸውን ያልገለፁ ዜጎች ቁጥር በርካታ መሆኑን የኮሚቴው አባላት ይገልፃሉ::

የመንግስትን ሃላፊነት የጉደለው ውሸትና ቅጥፈት ከማጋለጣቸው በተጨማሪ ያላግባብ ከመጠን ያለፈ ሃይል መጠቀሙን አብዛኛው ሟች ጭንቅላቱን መመታቱን

አረጋግጠዋል፡፡ እንደ ደርግ ዘመን ሁሉ በአንድ መቃብር በርካቶች መቀበራቸውን ያስረዳሉ፡፡

ከ60 ሺህ በላይ ዜጐች ሰብአዊነት በጐደለው ሁኔታ ታስረዋል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡ የራሱን መቃብር የቆፈረው ኢህአዴግ ይህንን ገበና ለማፈን ያላደረገው ነገር አልነበረም፡፡

የዚህ አረመኔ፣ ቀጣፊና ሃላፊነት የጐደለው ስርአት አገልጋይ በመሆን ህሊናቸውን ያቆሰሉ ዜጐች ቁጥር በርካታ ነው፡፡ በተቻላቸው መጠንና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይህን አረመኔአዊ ስርአት እንዲያጋልጡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይጠብቃቸዋል፡፡

ይህንን ሪፓርት የኢህአዴግ መንግስት ይፋ ላለማድረግ ቢያድበሰብሰውም ጭስና እውነት ቀዳዳ አያጣምና ለዓለም ህብረተሰብ ይፋ ሆንዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ መረጃ የማግኘት መብቱ የተገፈፈ ቢሆንም ባንድ ወይም በሌላ መልኩ ያገኘዋል፡፡

የዚህ ሪፓርት ሾልኮ መውጣት የስርአቱን ብልሹነት መግለጽ ብቻ ሳይሆን ለእስር የዳረጋቸውን የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጆች ለመወንጀል የሚጠቀመው የሀሰትና የቅጥፈት የተንኮልና የህገወጥ መረጃዎችን መሆኑንም በሚገባ ያመላክታል፡፡

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የኢህአዴግ መንግስት መጋለጡን ተገንዝቦ ትክክለኛውን ሪፓርት እንዲቀበል ይጠይቃል፡፡ ፓርቲአችን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመሆን በመሪዎቻችን በጋዜጠኞችና በሲቪል ማህበረሰብ መሪዎች ላይ የመሰረተው የሀሰት ክስ መረጃው ሁሉ ሀሰትና በበቀል የተመሰረተ መሆኑን ያምናል፡፡ ስለሆነም ፓርቲአችን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የዓለም ህብረተሰብ ኢህአዴግ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የታሰሩትን እንዲፈታ የሚአሳግጥበትን የፍርድ ሂደት እንዲአቋርጥ ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንጠይቃለን፡፡

በዚህ ጋጣሚ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርሰው የፓለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ተጠያቂው ኢህአዲግ መሆኑን በጥብቅ እናስገነዝባለን፡፡

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ**
**ጥቅምት 14 ቀን 1999**